# አስገራሚው የኢህአዴግ መግለጫ ሲዳሰስ

ታደሰ ብሩ

የኢህአዴግን የሚያዝያ 2003 መግለጫን አንብበውታል? ካላነበቡት እባክዎን መጀመሪያ አንብበው ይምጡ[1]። በእኔ ይሁንብዎ መግለጫውን ለማንበብ ያጠፉት ጊዜ አይቆጭዎትም፤ ቢያንስ በሳቅዎ ይካካስልዎታል።

አስገራሚ መግለጫ ነው። አርማ የለውም። የማን እንደሆነ የምናውቀው በአርዕስቱ፣ በይዘቱና በመጨረሻ የተፃፈው "የኢህአዴግ ምክር ቤት ጽ/ቤት" በሚለው ሃረግ ነው። ቀንም አልተፃፈበትም፤ መጨረሻ ላይ ቀኑ ለግምት ተትቶ "ሚያዝያ 2003" ተብሎ ተጽፎበታል። በመግለጫው ውስጥ ያሉት የሆሄያት ግድፈት ብዛት "ይህ መግለጫ ሲፃፍ የሚያጣድፍ ጉዳይ አጋጥሞ ነበር ይሆን?" ያስብላል።

መግለጫው አንባቢዎቹን ማዝናናት የሚጀምረው ከርዕሱ ጀምሮ ነው። በቀይ ቀለም

## ወቅታዊ መግለጫ

በኢህአዴግ ህዝባዊና ሳይንሳዊ አመራር የተቀጣጠለው የኢትዮጵያ ህዳሴ ጎዞ በመላው የሀገራችን ህዝቦች ተጠናክሮ ቀጥሏል!

ይላል።

እኔ ሳነበው በመጀመሪያ ጭንቅላቴ ውስጥ የመጣው "'ሳይንሳዊ አመራር' ምን ማለት ነው?" የሚለው ጥያቄ ነው። "አመራር" የሚለው ቃል የሚወክለው የእንግሊዝኛውን "Management" ከሆነ Scientific Management የነፍሬዴሪክ ቴይለር የ19ኛው ክፍለ ዘመን ንድፈሃሳብ ነው። በምንም ዓይነት ዛሬ "ወቅታዊ" ሊባል አይችልም። "አመራር" leadership ማለት ከሆነ ደግሞ Scientific leadership[2] ስለሚባል የህዝብ አመራር ሰምቼ አላውቅም።

"ሳይንሳዊ አመራር" የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ቅሪት ሳይሆን አይቀርም። አልባኒያዊ ኮሚኒስቶች "ሳይንሳዊ" የሚለውን ቃል ይወዱ ነበር። ወያኔ "ሳይንሳዊ" የሚለውን ቃል "ልማታዊ" በሚል ቃል መቀየር ችሎ ነበር። አሁን እንደለመደው "ልማታዊ አመራር" ከማለት ይልቅ "ሳይንሳዊ አመራር" ማለትን የመረጠው "ስለአመራሩ ምጡቅነት" ለማጋነን ፈልጎ ይመስለኛል።

ደስ ይበላቸው፤ ዳሰሳችንን ለመቀጠል "ሳይንሳዊ አመራር" ጥሩ አመራር ማለት ነው ብለን እንቀበል። ለመሆኑ የኢህአዴግን አመራር "ሳይንሳዊ" ያስባለው ምኑ ነው?

- አገራችን ወደብ አልባ በማድረጉ?
- ልጆችዋን በፈረቃ የምታበላ እናትን በፈጣን ልማት መዝሙር ማዝናናቱ?
- በትርጉም አልባ ጦርነቶች በ100 ሺህ የሚገመቱ ዜጎቻችንን ህይወት በመማገዱ?

---

1. http://aigaforum.com/articles/building_effective_leadership.pdf

2. Scinetific leadership በምርምር ተቋማት ውስጥ ያለው አመራር ማለት ሊሆን ይችላል። መግለጫው ግን ስለሱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው

- ህፃን ነቢዩ ሰለሞንን፣ ሽብሬ ደሳለኝን እና ሌሎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ህፃናትና ወጣቶችን በአጋዚ ጥይት እንዲጨፈጨፉ በማድረጉ?
- ኢትዮጵያዊው ገበሬ ተነቅሎ ለም መሬታችን ላይ ህንድ፣ ቻይናና አረብ ስለሰፈረበት?
- ከድምፀ-ወያኔ ሌላ በአገሪቱ ዜና እንዳይሰማና እንዳይታይ የሬድዮና የቴሌቪዥን ሞገዶችን የማፈን "አቅም" በመገንባቱ?
- የኢህአዴግ አባል ካልሆነ ወጣቱ ሥራ፤ ገበሬው ማዳበሪያ እንዳያገኝ ማድረግ በመቻሉ?
- የህዝቡን ትኩረት ለመለወጥ ሲል በመዘዘው የአባይ ግድብ የፕሮጀክት ሃሳብ ሰበብ የበርካታ ዜጎችን ንብረት በመዋጮ ስም መቀማት በመጀመሩ ነው?

ወይስ ....

- የመለስና አዜብ ዘመዶችና ተላላኪዎቻቸው በዘረፉት ገንዘብ ህንፃዎችን ገንብተው ስላሳዩን?
- በእርዳታና ብድር ከተገኘው ገንዘብ ላይ ተዘርፎ በተረፈችው ለታይታ የሚሆኑ መንገዶች ስለተሰሩ?
- አዜብ መስፍን የ80 ሚሊዮን ቤት እየሠራች በመሆኑ?
- የወያኔ ሹማምንትና የጦር መኮንንኖች በውጭ አገራት ሂሳብ ስላጠራቀሙ?
- እያንዳንዳቸው 800 000 ብር  የሚያወጡ የመለስ ዜናዊ ቢል ቦርዶች በየከተማው አደባባይ እንዲሰቀሉ የሚያደርግ በመሆኑ[3]?

መግለጫውን የፃፈው ሰው የኢህአዴግን አመራር ሳይንሳዊ ያስባሉትን ምክንያቶች ቢገልጽልን መልካም ነበር።

ቀጥሎ  ደግሞ  በመግለጫው ወደ አለ ባለ አንድ ዓረፍተ ነገር አንቀጽ ልውሰዳችሁ።

> *የኢህአዴግ ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መስመር የኢትዮጵያ ህዝቦች የጥንት ገናና ስልጣኔ ታሪክ፣ ሉአላዊ ማንነታቸውንና ነፃነታቸውን ለማስከበር ያደረጉትን ታላቅ የድል ትግልና ያላቸውን እምቅ አቅም ያገናዘበ እና ለህዝቦች ጥቅምና ብልጽግና የቆመ ድርጅት መሆኑን በማረጋገጥ ምላተ ህዝቡን ከጎኑ በማሰለፍ በሳል ሀገራዊና አህጉራዊ አመራር በመስጠት ላይ ነው።*

ይህን አንቀጽ መረዳት አስቸጋሪ ነው። ብዙ ነገሮች  ታጭቀውበታል፤ ተንዛዝቷል። ዝባዝኬዎቹን ትቼ ሁለት ነገሮች ላይ ትኩረት ልስጥ።

1. ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ገናና የስልጣኔ ታሪክን መቀበሉ "እልል!!!" የሚያሰኝ ነው። ጥያቄዎች ግን አሉኝ። የኢትዮጵያ ታሪክ የአንድ መቶ ዓመት ታሪክ ነው ሲል የቆየ ፓርቲ ዛሬ

[3] . በበኩሌ እነዚህ እያንዳንዳቸው 800 000 ብር ያወጣሉ የተባሉ ቢል ቦርዶች መሰቀላቸው በበኩሌ አልጠላሁትም። እንዲያውም ቶሎ ተሰቅለው በቅርቡ ከጥቂት  ወራት በኋላ በሚነሳው ህዝባዊ አመጽ ሲቀደዱ ማየት አጓጉቶኛል።

ይህ ሃቅ እንዴት ተከሰተለት? እንዴት አሁን ነፃነትን ስለማስከበር፣ ስለታላላቅ ድሎች እና እምቅ ኃይል ሊናገር ቻለ? እነዚህን ቃላት መናገርን ለመልመድ እንዴት ሃያ ዓመት ፈጀበት?

ኢህአዴግ ይህንን "ያገናዘበ እና ለህዝቦች ብልጽግና የቆመ ድርጅት" ነው መባሉ ግን እልልታችንን ብቻ ሳይሆን መገረማችንንም ያበላሽብናል- "ነጭ" ውሸት በመሆኑ!!!

2. ለመሆኑ መቼ ነው ኢህአዴግ አህጉራዊ አመራር ሲሰጥ የታየው? አንድ ፓርቲ አህጉራዊ አመራር የመስጠት መብት አለው ወይ?

መግለጫውን የፃፈው ሰው ፓርቲውና መለስ አንድ ናቸው ብሎ ስለሚያስብ ስለመለስ እያሰበ የፃፈው ሊሆን ይችላል። በመሠረቱ ይህ አስተሳሰብ ትክክል ነው። በኦፊሴል ስላልተቀበሉት ነው እንጂ መለስና ኢህአዴግ አንድ መሆናቸው ፀሃይ የሞቀው ሃቅ ነው።

መግለጫው ማለት የፈለገው መለስ ዜናዊን ወይንም የሱን አገዛዝ ማለት ከሆነስ አባባሉ እውነት ነው ወይ? መለስ ዜናዊን የአፍሪቃ መሪ አድርጎ ማቅረብ የኢትዮጵያ ቲሌቪዥን (ኢቲቪ) የእለት ተእለት ሥራ ነው። ሃቁን ለህዝብ የሚያቀርቡ የመረጃ አውታሮች በመታፈናቸው ኢቲቪ ደረቱን ነፍቶ ይዋሻል።

ሠንጠረዥ:  የሞ ኢብራሂም የ2010 የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Mauritius | 83.0 | 19 | Mali | 52.9 | 37 | Nigeria | 43.3 |
| 2 | Seychelles | 78.5 | 20 | Mozambique | 52.1 | 38 | Liberia | 43.2 |
| 3 | Botswana | 75.9 | 21 | Burkina Faso | 51.9 | 39 | Togo | 42.6 |
| 4 | Cape Verde | 75.5 | 22 | Malawi | 51.7 | 40 | Niger | 42.3 |
| 5 | South Africa | 71.5 | 23 | Libya | 51.5 | 41 | Congo | 42.0 |
| 6 | Namibia | 67.3 | 24 | Uganda | 50.8 | 42 | Angola | 39.3 |
| 7 | Ghana | 64.6 | 25 | Swaziland | 50.8 | 43 | Guinea-Bissau | 39.1 |
| 8 | Tunisia | 62.1 | 26 | Kenya | 50.5 | 44 | Côte d'Ivoire | 36.8 |
| 9 | Egypt | 60.5 | 27 | Gabon | 50.1 | 45 | Guinea | 35.6 |
| 10 | Lesotho | 60.1 | 28 | Madagascar | 48.7 | 46 | Equatorial Guinea | 34.7 |
| 11 | São Tomé & Príncipe | 58.2 | 29 | Comoros | 48.5 | 47 | Sudan | 32.9 |
| 12 | Benin | 56.6 | 30 | Djibouti | 48.5 | 48 | Central African Rep | 32.7 |
| 13 | Morocco | 56.6 | 31 | Rwanda | 47.2 | 49 | Zimbabwe | 32.7 |
| 14 | Senegal | 56.3 | 32 | Sierra Leone | 46.0 | 50 | Eritrea | 31.8 |
| 15 | Algeria | 55.2 | 33 | Burundi | 44.7 | 51 | Congo, Dem Rep. | 31.1 |
| 16 | Tanzania | 55.0 | 34 | Cameroon | 44.2 | 52 | Chad | 28.8 |
| 17 | Zambia | 54.9 | 35 | Ethiopia | 43.5 | 53 | Somalia | 7.9 |
| 18 | Gambia | 53.0 | 36 | Mauritania | 43.4 | | | |

ምንጭ:  የሞይ ኢብራኢም ኢንስቲቱት

*እንደ እውነቱ ከሆነ ግን መለስ ዜናዊ በአፍሪቃ እጅግ ደካማ ከሚባሉ መሪዎች አንዱ ነው። ለዚህ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ቢቻልም የ2010 እ.አ.አ. የሞ ኢብራሒምን የአፍሪቃ መንግሥታት የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስን ብቻ እንኳን መመልከት ይበቃል። የአፍሪቃ መንግሥታት አስተዳደር ተገምገመው ከ100 ያመጡት ውጤት ከላይ ባለው ሰንጠረዥ ተጠቃሏል።*

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ውጤት 43.5 ከመቶ ነው። ይህ ኢንዴክስ በበርካታ አመላካቾች ተሰልቶ የመጣ ነው። ይህ ውጤት የሚያኮራ ነው ወይስ የሚያሳፍር? ቀድሞ ኢትዮጵያ ከዚህ በተሻለ ደረጃ ላይ ነበረች። በመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያ የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ እያደር ቁልቁል የሚጓዝ ሆኗል። ጉራው ግን በተቃራኒ እያደር እየጨመረ ነው።

*ወደ መግለጫው እንመለስ*

*የኢትዮጵያ መንግስት በዓለም በትልቅነት ከተመዘገቡት ጥቂት ግድቦች አንዱና በአፍሪካ ደረጃ የመጀመሪያው የሆነውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለመገንባት ...*

እያለ መግለጫው ይቀጥላል።

"ከአፍሪቃ አንደኛ ከዓለም ሶስተኛ" የሚለው አባባል ምንጭ ከየት እንደሆነ ለማወቅ ከዚህ በፊትም ሞክሬ አቅቶኛል። ስለዚህ አባባል ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ስናወራ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ በጉብዝናው ያደንቁት የነበረው የኬሚስትሪ አስተማሪያቸው በኬሚስትሪ ከአፍሪቃ አንደኛ ከዓለም ሶስተኛ እንደሆነ በስፋት ይወራ እንደነበርና እሱም ይኸንን አምኖ ተቀብሎ እንደኖረ ነግሮኛል።

"ከአፍሪቃ አንደኛ ከዓለም ሶስተኛ" በልጅነት የለመድነው ማነፃፀሪያ ነው። የሚያሳዝነውና የሚገርመው እንዲህ ዓይነቱ በማስረጃ ያልተደገፈን ጉራ በፓርቲ መግለጫነት መውጣቱ ነው። በወጉ ንድፉ እንኳን ስለመሰራቱ አጠራጣሪ የሆነውን ግድብ "በአፍሪቃ አንደኛ ነው፤ በዓለም ከታላላቆቹ አንዱ ነው" እያሉ መሬት ያሉ ነገሮችን ከሌለ ነገር ጋር ማወዳደር ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው?

***

የሚያዝያ 2003ቱ የኢህአዴግ መግለጫ በጉራና በስህተቶች ብዛት የተለየ ባህርይ ይዟል። ስለ "ሳይንሳዊ አመራር" ከዚህ መግለጫ በፊት ስለመነሳቱ በበኩሌ አላውቅም። ኢህአዴግ አህጉሩን እየመራ ስለመሆኑ በመግለጫ ሲቀርብ ሳይም ይህ የመጀመሪያዬ ነው።

በመግለጫው ውስጣችን እያረረም ቢሆን እንሳቅ። ይህ ማላገጥ ግን መብቃት አለበት። ይህ ማላገጥ እንዲያበቃ የምንፈልግ ሁሉ ሙሉ ኃይላችንን በጠላታችን በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ በማድረግ በጋራ የመነሻ ጊዜዓችን አሁን ነው። ማላገጥ በቃ እንበል!

በቃ- ጋዬ!!!